በኢስላም ውስጥ ከርሶ ውጪ ስለርሱ አንድንም ሰው የማልጠይቀው የሆነን አንድን ንግግር ንገሩኝ አልኳቸው። እርሳቸውም 'በአላህ አምኛለሁ በል ከዚያም ቀጥ በል።' አሉኝ

ከአቡ ዓምር አቡ ዓምራ ነውም ተብሏል: ከሱፍያን ቢን ዐብደላህ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ
አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! በኢስላም ውስጥ ከርሶ ውጪ ስለርሱ አንድንም ሰው የማልጠይቀው የሆነን አንድን ንግግር ንገሩኝ
አልኳቸው። እርሳቸውም 'በአላህ አምኛለሁ በል ከዚያም ቀጥ በል።' አሉኝ" [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ሶሐቢዩ ሱፍያን ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ‐ ስለርሱ አንድንም ሳይጠይቅ እርሱን አጥብቆ የሚይዘው የሆነን የኢስላምን ሀሳቦች የጠቀለለ የሆነን ንግግር እንዲያስተምሩት ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጠየቀ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለርሱ "አላህ ብቻውን ጌታዬ፣ አምላኬ፣ ፈጣሪዬ፣ አጋር የሌለው በእውነት የሚመለከው ብቸኛ መሆኑን አረጋግጫለሁ። በል!" አሉት። ከዚያም ለአላህ ትእዛዝ የአላህን ግዴታዎች በመፈፀምና የአላህን ክልከላዎች በመተው ታዛዥ ይሁን፤ በርሱ ላይም ይዘውትር።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/66524